# በኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት

# በልዩ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የውስጥ መመሪያ

የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት
ETHIOPIAN BIODIVERSITY INSTITUTE

ሰኔ 2018 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

**መግቢያ**

የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ለሀገራችን የተፋጠነ እድገት መሰረት የሆነውን ዘርፈ ብዙ የብዝሀ ሕይወት ሀብት ማንበርና በምርምርና ጥናት በተደገፈ አሠራር በተገቢው መንገድ እንዲታወቅ፣ አሁን ያለው የብዝሀ ህይወት ሀብት እንዳይመናመን የሚያስችል ዘላቂ አጠቃቀም እንዲተገበር እና ከብዝሀ ሕይወት የሚገኝ ጥቅም ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እየሰራ ያለ ተቋም ነው፡፡

እነዚህ መጠነ ሰፊ ሥራዎች በመንግስት መደበኛ በጀት የሚከናወኑ ሲሆን፤ የተወሰኑት ደግሞ በብዝሀ ህይወት ላይ በሚሰሩና ተመሳሳይ ዓላማ ባላቸው ተቋማት በሚገኝ ልዩ ፈንድ በሚደገፉ ፕሮጀክቶች የሚተገበሩ በመሆናቸው፤

እነዚህ ፕሮጀክቶች በጊዜ ገደብ የሚፈጸሙ ከመሆናቸውም በላይ አደረጃጀታቸው ከመደበኛው ወይም በመንግስት ከሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ለየት ያለና ልዩ ትኩረት የሚሹ፣ እንዲሁም ማህበረሰቡ ድረስ ወርደው የሚፈጸሙ በመሆናቸው አሰራራቸው ግልጽነት፣ ወጥነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን በማስፈለጉ፤

የፕሮጀክቶችን ዓላማ በሕጋዊ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ባለው አሰራር ለማስፈጸም፣ የልዩ ፈንድ ድጋፍ ለታለመለት ዓላማ ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ፣ በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015፣ በኢንስቲትዩቱ መቋቋሚያ ደንብ ቁ. 291/2005 እና በሌሎች ተፈጻሚ ሕጎች መሠረት የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ወጥነት ያለው እንዲሆን ይህ የውስጥ መመሪያ ተሻሽሎ ወጥቷል፡፡

**የዚህ መመሪያ አስፈላጊነት**

1. የኢንስቲትዩቱን ተልዕኮ ለማስፈጸም የሚያግዙ በልዩ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን በታቀደላቸው ጥራት፣ መጠንና ጊዜ በአግባቡ እንዲተገበሩ ለማስቻል፤
2. የኢንስቲትዩቱ አመራሮችና እና ባለሙያዎች የመንግስትን ፕሮግራም የሚደግፉ፣ ለሀገርና ለተቋሙ ሃብት ሊያስገኙና አቅምን ሊገነቡ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን እንዲቀርጹ፣ ፈንድ እንዲያፈላልጉና እንዲተገብሩ ለማበረታታት፤
3. በኢንስቲትዩቱ የሚተዳደሩና በቀጥታ ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስፈን፤
4. ውጤታማ አፈጻጸምን በማረጋገጥ በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ከሚገኙ ተባባሪ ተቋማት ጋር በቅንጅት የመስራት ባህልን ለማጠናከር፤

ከርታ ከስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

5. የማትጊያ፣ የአገልግሎት፣ የሥልጠና፣ የዶክመንት ዝግጅት እና ሌሎች ሕጋዊ ክፍያዎች ከፕሮጀክት ስምምነት፣ ከተፈቀደ በጀት፣ ከግብር ሕግ እና ከተፈጻሚ ሌሎች የመንግሥት ህጎችና መመሪያዎች ጋር ተጣጥመው እንዲተገበሩ ለማድረግ፣
6. በአዋጅ ቁጥር 1298/2015 መሠረት ተቋማዊ ጥቅምን፣ ግልጽነትን እና የጥቅም ግጭት መከላከልን በሚያሰፍን መልኩ አሰራሮች እንዲተገበሩ ለማስቻል ነው፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1፡ አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት በልዩ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የውስጥ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2፡ ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ኢንስቲትዩት"** ማለት የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ሲሆን፣ ዋና መስሪያ ቤቱንና በስሩ የሚገኙ የብዝሀ ህይወት ማዕከላትን፣ የዕፅዋት አፀዶችንና ዱፕሊኬት ጅን ባንክን ያጠቃልላል፡፡
2. **"ልዩ ፈንድ"** ማለት ከመደበኛ የመንግሥት በጀት እና ከልማት አጋር ከተገኘ ብድርና እርዳታ በተለየ መልኩ ለተወሰነ የምርምር ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በፕሮጀክት ስምምነት፣ በፀደቀ በጀት ወይም በሕጋዊ ማረጋገጫ መሠረት ከውጭ ወይም ከሀገር ውስጥ ምንጮች፣ ከፋውንዴሽኖች፣ ወይም መንግሥታዊ ድርጅቶች የሚገኝ ድጋፍ ማለት ነው፡፡
3. **"በልዩ ፈንድ የሚደገፍ ፕሮጀክት"** ማለት በልዩ ፈንድ የገንዘብ፣ የቴክኒክ ወይም የዓይነት ድጋፍ ተመስርቶ፣ በኢንስቲትዩቱ ወይም ከኢንስቲትዩቱ ጋር በትብብር የሚተገበር፣ በፕሮጀክት ስምምነት፣ በተፈቀደ በጀት፣ እና በዚህ መመሪያ የሚመራ ፕሮጀክት ማለት ነው፡፡
4. **"የፕሮጀክት አስተባባሪ/ማናጀር** (Project Coordinator/Manager)" ማለት በልዩ ፈንድ የሚደገፍ ፕሮጀክትን እንዲያስተባብር በኢንስቲትዩቱ የተመደበ፣ ወይም የተቀጠረ ባለሙያ፣ ወይም ፕሮጀክቱን ተጻጽፎ ያመጣ ባለሙያ ነው፡፡

ጋርታ ከስኬ ከልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

5. **"የፕሮጀክት ተመራማሪ** (Project Investigator)" ማለት የፕሮጀክቱን ዓላማ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን መሠረት ባደረገ ግልጽ መስፈርት ተወዳድሮ በመመደብ፣ የፕሮጀክት አስተባባሪውን እንዲያግዝ የሚመደብ ተመራማሪ ነው፡፡

6. **"ፕሮጀክት ማኔጅመንት ቡድን"** ማለት በፕሮጀክት ሰነድ፣ በፀደቀ የሥራ ድርሻ እና በተፈቀደ በጀት መሠረት በፕሮጀክት ቀረጻ፣ ትግበራ፣ ፋይናንስ፣ ግዥ፣ ንብረት አስተዳደር፣ ክትትል፣ ግምገማ፣ ሪፖርትና ኦዲት ሂደት የሚሳተፉ የተቋሙ ወይም በሕጋዊ ውል የተመደቡ ባለሙያዎች ናቸው፡፡

7. **"የልማት አጋር"** ማለት በአገራችን በሁለትዮሽ ወይም በባለብዙ ወገን ስምምነቶች መሠረት ለልማት ለፕሮግራሞች ወይም ለፕሮጀክቶች የፋይናንስ፣ የቴክኒክ ወይም የዓይነት ድጋፍ በብድር፣ በእርዳታ ወይም በትብብር መልክ የሚሰጥ ተቋም ማለት ነው፡፡

8. **"ውሎ አበል"** ማለት በፕሮጀክት ወይም በተቋማዊ ተልዕኮ ምክንያት ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ በሚካሄድ መስክ ጉዞ፣ ስልጠና፣ አውደ ጥናት ወይም ሌላ ተግባር ላይ ለሚሳተፍ ሰው ለቀን የምግብና ተዛማጅ የጉዞ ወጪዎች ማካካሻ የሚከፈል ማለት ነው፡፡

9. **"አስተዳደራዊ ወጪ"** ማለት በፕሮጀክት ስምምነት እና በፀደቀ በጀት መሠረት ለተቋማዊ የፕሮጀክት አስተዳደር፣ ፋይናንስ፣ ኦዲት፣ ግዥ፣ ክትትል፣ ሪፖርት እና ሎጂስቲክስ የሚውል ወጪ ነው፡፡

10. **"ማትጊያ ክፍያ** (top-up)" ማለት በፕሮጀክት ስምምነትና በፀደቀ በጀት ለተረጋገጠ ተጨማሪ ሥራ ወይም በፕሮጀክቱ ላይ በግልጽ የተመደበ የሥራ ጊዜ ሊፈጸም የሚችል ክፍያ ማለት ነው፡፡

11. "ደመወዝ" ማለት በፕሮጀክት ስምምነቱ መሰረት የበጀት መስመር የተቀመጠለት እና ሙሉ ጊዜውን ወይም አብላጫውን ጊዜውን በፕሮጀክቱ ስራዎች ላይ ለሚያውል ግለሰብ የሚፈጸም ክፍያ ነው፡፡

12. "የጋራ መገልገያ ወጪ (Over head cost)" ማለት በፕሮጀክት ስምምነቱ መሠረት ወይም በስምምነቱ በግልፅ ካልተቀመጠ የጠቅላላ በጀቱ 10% ሆኖ ለጋራ አገልገሎች የሚውል ነው፡፡

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

**አንቀጽ 3፡ ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ በኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት በልዩ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑና በአግባቡ እንዲፈጸሙ ለማስቻልና ባለሙያዎችን ለማነሳሳትና ለማበረታታት ነው፡፡

**አንቀጽ 4፡ የተፈፃሚነት ወሰን**

የዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት ወሰን በኢንስቲትዩቱ የሚተዳደሩ፣ በቀጥታ ወይም ከሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር የሚተገበሩ በልዩ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በልዩ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም

**አንቀጽ 5፡ ተግባራዊ የሚደረጉ ሕጎች**

በልዩ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በተመለከተ በፕሮጀክት ሰነዶች የተመለከቱ አሰራሮችና አፈጻጸሞች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አግባብነት ያላቸው የመንግሥት አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ተፈጻሚ ይደረጋሉ፡፡

**አንቀጽ 6፡ የፕሮጀክት ተጠሪነት**

በልዩ ፈንድ የሚደገፍ ፕሮጀክት ተጠሪነቱ እንደ ፕሮጀክቱ ዓይነት፣ የሥራ ዘርፍ እና የስምምነት ሰነዱ መሠረት ለኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለተወከለው የሥራ ክፍል ኃላፊ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 7፡ የፕሮጀክት አስተባባሪ ስለመሰየም**

1. የፕሮጀክት አስተባባሪ የሚሰየመው በፕሮጀክት ሰነዱ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡ ሰነዱ ላይ የተገለጸ ነገር ከሌለ በውድድር ወይም በበላይ ኃላፊው ሊሰየም ይችላል፡፡
2. የፕሮጀክት አስተባባሪ የሚሰየመው ከኢንስቲትዩቱ ነው፡፡ ሆኖም ሙሉ ጊዜ የፕሮጀክት ደመወዝ የሚከፈለው ሰው ከተመሳሳይ ፕሮጀክት ላይ ተጨማሪ የማትጊያ መብት አይኖረውም፡፡
3. ተመራማሪዎች ፕሮጀክቶችን ተፃፅፈው እንዲያመጡና ተሳትፏቸውን ለማሳደግ፣ የትምህርት ዝግጅትን፣ የምርምር እና የማኔጅመንት ልምድን በማገናዘብ የማስተባበር ተሳትፏቸው እንደሚከተለው ይሆናል፦
   - 3.1. እስከ ተባባሪ ተመራማሪ የሥራ ደረጃ የሚገኙ አንድ ፕሮጀክት በማስተባበር ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

3.2. በተመራማሪ I እና II የሥራ ደረጃ የሚገኙ በአንድ ጊዜ እስከ ሁለት የሚደርሱ ፕሮጀክቶችን በአስተባባሪነት ሊመሩ ይችላሉ፡፡

3.3. በከፍተኛ እና መሪ ተመራማሪ የሥራ ደረጃ የሚገኙ በአንድ ጊዜ እስከ ሦስት ፕሮጀክቶችን ሊመሩ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ይህ በተቋሙ የበላይ ሀላፊ የስራ ጫናን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰናል፡፡

3.4. በቁጥር ተራ 3.3 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ተመራማሪ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ ሆኖ አንድን ፕሮጀክት የሚያስተባብር ከሆነ በሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ የፕሮጀክት ተመራማሪነት እንጂ የአስተባባሪነት ክፍያ አይኖረውም፡፡ ሆኖም ከአንድ ፕሮጀክት በላይ ፈንድ በውድድር ያገኘ ተመራማሪ ካገኛቸው ፕሮጀቶች ላይ በውል በተያዘው በጀት መሰረት ከፍ ያለ ደሞዝ የሚያስገኝለት ወይም የተሻለ የፕሮጀክት ዕድሜ ባለው ፕሮጀክት ላይ የመመደብ ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

3.5. አንድ ተመራማሪ /ባለሙያ/ ኃላፊው ማትጊያ (top-up) የሚከፈለው፣ ክፍያው ከተመራማሪው/ባለሙያው/ኃላፊ ደሞዝና ጥቅማጥቅም ድምር ያነሰ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ተመራማሪው/ባለሙያ/ኃላፊው ከአንድ ፕሮጀክት የሚያገኘው ክፍያ ከደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ድምር የሚበልጥ ከሆነ ክፍያው ወደ ደሞዝ ተቀይሮ ይከፈለዋል፡፡

3.6. ማንኛውም የልዩ ፈንድ ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ክፍያ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ጸድቆ በሰው ኃብት ሲመዘገብ በፕሮጀክቶች ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ክፍያ ሰነድ (payroll) መሰረት ክፍያ ይፈጸማል፡፡

4. የፕሮጀክት አስተባባሪው በስራው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ በማይገኝበት ወቅት የፕሮጀክት ተመራማሪው ይወከላል፡፡

5. አስተባባሪው ከአንድ ወርና ከዚያ በላይ በስራው ላይ የማይገኝበት ሁኔታ ሲኖር፣ ዋና ዳይሬክተሩ ፕሮጀክቱን በጊዜያዊነት የሚያስተባብር ብቁ ሰው ይወክላል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አስተባባሪው ሥራውን መልቀቁ ወይም በሌሎች ምክንያቶች በሥራ ገበታ ላይ የማይገኝ መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ ፕሮጀክቱን በቋሚነት የሚያስተባብር ባለሙያ ይመደባል፡፡

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

**አንቀጽ 8፡ የፕሮጀክት አስተባባሪ ተጠሪነት**

የፕሮጀክት አስተባባሪ ተጠሪነቱ ለኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ለተወከለ የስራ ክፍል ኃላፊ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 9፡ የፕሮጀክት ሥራን በትብብር ስለመፈጸም**

1. የፕሮጀክት አስተባባሪው በፕሮጀክት ሰነዱ ላይ በተቀመጠው እንዲሁም በበላይ አመራሩ በሚሠጠው አቅጣጫ መሠረት ፕሮጀክቱን ይመራል ወይም ያስተዳድራል፡፡
2. በኢንስቲትዩቱ የሚመለከተው የሥራ መሪ በፕሮጀክት ሰነዱ የተቀመጡ የፕሮጀክት ሥራዎች ከመደበኛ ሥራዎች ጋር ተቀናጅተው በጥራት፣ በመጠንና በጊዜ እንዲተገበሩ የማሳለጥ፣ የድጋፍ፣ የክትትልና የግምገማ ሥራን ይመራል ወይም ያስተባብራል፡፡

**አንቀጽ 10፡ የፕሮጀክት ፋይናንስ፣ ንብረት፣ ዕቅድ፣ ሪፖርት፣ ኦዲት እና የክፍያ ማስፈጸሚያ ሥርዓት**

1. የፕሮጀክት ፋይናንስ አስተዳደር በፕሮጀክት ሰነድ፣ በተፈቀደ በጀት፣ በፕሮጀክት ስምምነት፣ በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር፣ የግዥ፣ የግብር እና ሌሎች ተፈጻሚ ሕጎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

2. በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት የፕሮጀክት ፋይናንስ ዘርፍ የሰው ኃይል እንዲሟላ ይደረጋል፡፡ የፕሮጀክት ፋይናንስ ዘርፍ ተጠሪነቱ ለግዥና ፋይናንስ ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ የቡድን መሪ፣ የበጀት ተቆጣጣሪ እና የፕሮጀክቱ ፋይናንስ ሠራተኛ ይኖራቸዋል፡፡

3. የፕሮጀክት ዕቅድ፣ የፊዚካል፣ የፋይናንስና የግዥ አፈፃፀም፣ የንብረት እና የኦዲት ሪፖርት በፕሮጀክት አስተባባሪው ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው የሥራ መሪ ወይም ለበላይ አመራር ይቀርባል፡፡ ለድጋፍ ሰጪ አካል፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር ወይም በሕግ ለተፈቀደላቸው ተቆጣጣሪ አካላት የሚቀርብ ሪፖርት በተያዘለት ጊዜና በሚፈለገው ሁኔታ ይዘጋጃል፡፡

4. የፕሮጀክት መረጃዎች፣ ቫውቸሮች፣ የክፍያ መዝገቦች፣ የውሎ አበል መዝገቦች፣ የንብረት ርክክብ ሰነዶች እና የኦዲት ሪፖርቶች በተፈጻሚ የፋይናንስ ሕግ እና በተቋሙ የሰነድ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በተቋሙ ይቀመጣሉ፡፡

5. የፕሮጀክቱ ንብረት በዋናነት የፕሮጀክት ተግባራትና ዓላማ ማስፈጸሚያ የሚውል ሆኖ፣ አጠቃቀሙና አስተዳደሩ በመንግሥት ሕግ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡ ሆኖም ፕሮጀክቱ ጊዜው ሲያልቅ ወይም በሆነ ምክንያት ቢቋረጥ ንብረቱ ወደ ጋራ መጠቀሚያ ይገባል፡፡

6. ማንኛውም የማትጊያ፣ የአገልግሎት፣ የሥልጠና፣ የጥናት አቅራቢነት፣ የዶክመንት ዝግጅት ወይም ሌላ ክፍያ በተፈጻሚ የገቢ ግብር፣ ተቀናሽ ግብር እና ሌሎች የግብር ሕጎች መሠረት ተቀናሽ ተደርጎ ይፈጸማል፡፡



ዶ/ር ታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

7. ለውጭ አማካሪዎች፣ ለሎጂስቲክስ አቅራቢዎች፣ ለሶፍትዌር/ዳታቤዝ አበልጻጊዎች እና ለሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች የሚደረግ ክፍያ በግዥ ሕግ፣ በአገልግሎት ውል፣ በTIN፣ በደረሰኝ እና በውጤት ተቀባይነት ማረጋገጫ መሠረት ይፈጸማል፡፡

8. ለክፍያ የሚቀርብ ጥያቄ የተፈቀደ የሥራ ድርሻ፣ የጊዜ መዝገብ፣ የሥራ ውጤት ማረጋገጫ፣ የበጀት መስመር ማረጋገጫ፣ የውስጥ ኦዲት ማረጋገጫ እና የግብር ተቀናሽ ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

9. በፕሮጀክት ስምምነት የተፈቀደ አስተዳደራዊ ወጪ ካለ፣ ወደ ኢንስቲትዩቱ ሕጋዊ ሂሳብ ገቢ ተደርጎ ለፋይናንስ፣ ለኦዲት፣ ለግዥ፣ ለንብረት አስተዳደር፣ ለክትትልና ለሎጂስቲክስ የፕሮጀክት ድጋፍ ወጪዎች ይውላል፡፡

## አንቀጽ 11፡ የፕሮጀክት የሰው ኃይል ቅጥር

1. የፕሮጀክት የሰው ኃይል ቅጥር በፕሮጀክት ሰነዱ በተመለከተው መሠረት በፕሮጀክት አስተባባሪው ተጠይቆ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሲፀድቅ፣ በፕሮጀክት ሰነድ፣ በፀደቀ ዕቅድ፣ በበጀት እና በተፈጻሚ ሕጎች መሠረት ይፈጸማል፡፡
2. ማንኛውም ልዩ ፈንድ አጠቃላይ በጀቱ 500 ሺህ ዶላር እና ከዚያ በላይ ከሆነ እና ቢያንስ ሁለት ዓመታት እድሜ የሚቆይ ከሆነ አንድ አካውንታንት እና አንድ የክትትልና ግምገማ ባለሙያ በደሞዝ ወይም ማትጊያ ክፍያ ይመደባሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## በልዩ ፈንድ በሚደገፉ ፕሮጀክቶች የሚፈጸሙ ልዩ ልዩ ክፍያዎችና ጥቅማጥቅሞች

## አንቀጽ 12፡ በፕሮጀክት ትግበራ ላይ ለሚሳተፉ አመራሮችና ባለሙያዎች የሚፈፀም ክፍያ

1. ለፕሮጀክት ማስተባበሪያ እና ትግበራ ማትጊያ (Staff time, Personnel or Honorarium) የሚያዘው በጀት ከጠቅላላው በጀት 25 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡ ሆኖም የፕሮጀክቱ ጠባይ አስገዳጅ ሆኖ ሲገኝ የበላይ ኃላፊን በማማከር በልዩ ሁኔታ እስከ 30 በመቶ ከፍ ሊል ይችላል፡፡

2. በልዩ ፈንድ ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ለማሳለጥና ተጠባቂ ውጤቶች በጥራትና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲቀርቡ ለማድረግ፣ በፕሮጀክት ለሚሳተፉ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የገቢ ግብር የሚከፈልበት ተመጣጣኝ ማትጊያ ይከፈላል፡፡ ክፍያው የሚፈፀመው ፕሮጀክቱ በቂ በጀት ካለውና በስምምነት ሰነዱ ውስጥ ማትጊያ ወይም ደሞዝ ወይም የሰው ኃይል (Personnel) በሚል በግልፅ ሲመደብ ብቻ ነው፡፡

3. በልዩ ፈንድ የሚተገበር ፕሮጀክትን ለሚመራ አስተባባሪ/ማናጀር(Project Coordinator/Manager)፣ ዋና ተመራማሪ (Principal Investigator)፣ ተባባሪ ተመራማሪ (Co-Principal Investigator) እና

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

የፕሮጀክት ተጠሪ (Focal Person) በፕሮጀክቱ የውል ስምምነት ሰነድ በተቀመጠው መሠረት ደመወዝ ወይም የማበረታቻ ክፍያ ይከፈላል።

4. ለፕሮጀክት ማስፈፀሚያ በቂ የሰው ኃይል (Personnel) በጀት ተመድቦ ነገር ግን አፈፃፀሙ በፕሮጀክቱ የውል ስምምነት ሰነድ በጥቅል የተቀመጠ ከሆነ፣ ወይም ፕሮጀክቱን በገንዘብ የሚደግፈው አጋር ድርጅት በኢንስቲትዩቱ የውስጥ መመሪያ እንዲከናወን ከገለጸ፣ ወይም ዝርዝሩ በግልጽ ያልተመለከተ ከሆነ፣ የማትጊያ ክፍያው እንደሚከተለው ይፈፀማል።

4.1. ለፕሮጀክት አስተባባሪ/ማናጀር (Project Coordinator/Manager) ወይም ዋና ተመራማሪ (Principal Investigator) ለእያንዳንዳቸው በወር ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) ይከፈላል፤

4.2. ለተባባሪ ተመራማሪ (Co-Principal Investigator) በወር ብር 20,000 (ሃያ ሺህ) ይከፈላል።

4.3. ለፕሮጀክት ተጠሪ (Focal Person) በወር ብር 10,000 (አሥር ሺህ) ይከፈላል።

5. የተቋሙ የበላይ አመራር፣ የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የስልጠና፣ ማማከር፣ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ እና የድጋፍ ሰጪ ሥራ አስፈጻሚዎች ከመደበኛው ሥራቸው በተጨማሪ ለፕሮጀክቶች ትግበራ ውጤታማነት፣ ለፋይናንስ ቁጥጥር፣ ለኦዲት ክትትል እና ለተቋማዊ አስተዳደር ጉልህ ሚና እንዳላቸው በሚታመንበት ጊዜ፣ ፕሮጀክቶች ለአጠቃላይ አስተዳደራዊ እና የጋራ መገልገያ ወጪዎች (Overhead Cost) ከሚሰበሰብ ቋት እንደሚከተለው ሊከፈል ይችላል።

5.1. ለዋና ዳይሬክተር እና ለምክትል ዋና ዳይሬክተር እያንዳንዳቸው በወር ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ)።

5.2. ለስልጠና፣ ማማከር፣ ፕሮጀክት ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ በወር ብር 20,000 (ሃያ ሺህ)።

5.3. ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ፣ ፣ በወር ብር 10,000 (አሥር ሺህ) ይከፈላል።

5.4. ለሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ በወር ብር 10,000 (አሥር ሺህ)።

5.5. ለስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ በወር ብር 10,000 (አሥር ሺህ)።

5.6. ለግዥና ፋይናንስ ስራ አስፈፃሚ 20,000 (ሃያ ሺህ) እና ለልዩ ፈንድ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ቡድን መሪ በወር ብር 10,000 (አሥር ሺህ) ይከፈላል።

5.7. ከቁጥር ተራ 5.1 እስከ 5.6 ያሉ ክፍያዎች የሚፈፀሙት ለጋራ መገልገለያ ወጪዎች በወሩ ውስጥ የተሰበሰበውን 30% መብለጥ አይችልም:: አነስተኛ ገንዘብ ተሰብስቦ ከሆነ እንደ መጠኑ ተጣጥሞ የሚከፈል ይሆናል።

5.8. የብዝሀ ህይወት ማዕከላት በልዩ ፈንድ ከሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ለአጠቃላይ አስተዳደራዊ እና የጋራ መገልገያ ወጪዎች (Overhead Cost) የሚያሰባስቡት ዓመታዊ ገንዘብ ብር 200,000 (ሁለት



ካርታ ካሰኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

መቶ ሺ.ህ) እና ከዚያ በላይ ሲሆን፣ ለማዕከል ዳይሬክተር በወር ብር 9000 (ዘጠኝ ሺ.ህ)፣ ለፋይናንስ የሥራ ሂደት ተጠሪ እና ለፕሮጀክት አካውንታንት እያንዳንዳቸው በወር ብር 4,000 (አራት ሺ.ህ) የማትጊያ ክፍያ ይከፈላል፡፡

5.9 ከላይ ከተ.ቁ 5.1-5.8 የተዘረዘሩት ክፍያዎች ተግባራዊ የሚሆኑት በፕሮጀክት ስምምነቱ መሠረት የፕሮጀክት “Over-head Cost” ከተያዘ ወይም አስተዳደራዊ ወጪ ለመሸፈን ከተፈቀደ በጀት ላይ ብቻ ነው፡፡

5.10. በዚህ አንቀጽ 12 የተመከቱትን የደሞዝ /ጥቅማጥቅም ክፍያዎች የፕሮጀክቶች የፋይናንስ ቡድን መሪ ከሥልጠና ማማከርና ፕሮጀክቶች ክትትል መሪ ሥራ አስፈፃሚ በሚቀርብለት ዝርዝር መሠረት በጀት መኖሩን እያረጋገጠ የመክፈያ ሰነድ (payroll) ለሚመለከተው ኃላፊ ይቀርባል፡፡

**አንቀጽ 13፡ ፕሮፖዛል አዘጋጅተው ፈንድ ለሚያመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚፈጸም የማበረታቻ ክፍያ**

**13.1 ፕሮፖዛል አዘጋጅተው ፈንድ ለሚያመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚከፈል የማበረታቻ ክፍያ የሚከናወነው በደሞዝ መልክ ወይም ከደሞዝ በተጨማሪ (top-up) መልክ ሆኖ በአንቀጽ 7 እና በአንቀጽ 12 በተቀመጠው ስሌት መሰረት ይሆናል፡፡**

13.2 ከልዩ ፈንድ ምንጮች ፈንድ በማፈላለግ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ገንዘብ ላስገኙ ግለሰቦች የሚከፈለው ደሞዝ ወይም ማበረታቻ (top up) የሚከፈለው በተፈቀደ በጀት መስመር እና በፕሮጀክት ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

13.3 በፕሮጀክት ስምምነቱ ደሞዝ ወይም የማትጊያ ክፍያ የሚሰላው/የሚያዘው በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሆናል፡፡

1. ፈ እስከ 100,000 ዶላር ከሆነ፦ ፈ × 0.05፣’ፈ’=የተገኘ የፈንድ መጠን በዶላር

2. ፈ በ 100,000 እና 500,000 ዶላር መካከል ከሆነ፦ 5,000 + ((ፈ - 100,000) × 0.04)

3. ፈ በ 500,000 እና 1,000,000 ዶላር መካከል ከሆነ፦ 21,000 + ((ፈ - 500,000) × 0.03)

4. ፈ ከ 1,000,000 በላይ ከሆነ፦ 36,000 + ((ፈ - 1,000,000) × 0.02)

5. የሚከፈለው የደሞዝ የማትጊያ መጠን በፕሮጀክቱ የተፈቀደ መሆን፣ ፈንዱ በሕጋዊ መንገድ በተቋሙ ባንክ አካውንት ውስጥ ገቢ መሆን፣ በተቋሙ የበላይ ኃላፊ መጽደቅ እና በዚህ መመሪያ የተመለከቱት የግብርና የክፍያ መስፈርቶች መሟላት ላይ ይመሠረታል፡፡

6. የፈንድ ማፈላለግ ሂደቱ በቡድን የተከናወነ ከሆነ /የደሞዝ/ የማትጊያው ክፍያ በአባላቱ በተረጋገጠ የሥራ ድርሻ እና በበላይ ኃላፊ ውሳኔ መሠረት ለአስተባባሪ ፣ ለተመራማሪ በሚል ይከፋፈላል፡፡



ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

**አንቀጽ 14፡ ዶክመንት አዘጋጆች፣ ጥናት አቅራቢዎች እና ስልጠና ሰጪዎች ክፍያ**

1. የሥልጠና፣ የውጤት ማቅረብ፣ የማኑዋል ዝግጅት ወይም የዳታቤዝ/መተግበሪያ ማበልጸግ ክፍያ በፕሮጀክቱ ሰነድ፣ በተፈቀደ በጀት እና በተረጋገጠ የሥራ ውጤት መሠረት ይፈጸማል፡፡

2. ከፕሮጀክቱ የሚመነጩ ውጤቶች እንደ አስፈላጊነቱ በአዕምሯዊ ንብረት መብቶች አዋጅ ቁጥር 1298/2015 መሠረት ይጠበቃሉ፡፡

3. በአውደ ጥናት ላይ የጥናት ውጤቶችን ለሚያቀርቡ የውስጥም ሆነ የውጭ ባለሙያዎች ለአንድ ጽሑፍ 100 የአሜሪካ ዶላር ይከፈላል፡፡

4. ክህሎትን መሠረት በማድረግ ስልጠና ለሚሰጡ ባለሙያዎች፡ ከ1 እስከ 3 ቀን 83 የአሜሪካ ዶላር፣ ከ4 እስከ 7 ቀን 170 የአሜሪካ ዶላር፣ ከ7 ቀን በላይ 167 የአሜሪካ ዶላር ይከፈላል፡፡

5. በፕሮጀክት ለተያዙ አውደ ጥናቶች እና ስልጠናዎች የተመደቡ አስተባባሪዎች፣ ብዛታቸው ከ1 እስከ 5 በመሆን፣ ለእያንዳንዳቸው 67 የአሜሪካ ዶላር ይከፈላል፡፡

6. የመተግበሪያ፣ ዳታቤዝ እና ድረ ገጽ ለሚያበለጽጉ ባለሙያዎች ክፍያ እንደ ፕሮጀክቱ ፈንድ መጠን፣ የሥራ ውጤት እና የበጀት መስመር በተቋሙ የበላይ አመራር ይወሰናል፡፡

7. ሳይንሳዊ ዶክመንቶችን፣ ሪፖርቶችንና ማኑዋሎችን ለሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ለእያንዳንዳቸው 167 የአሜሪካ ዶላር ይከፈላል፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ን ዑስ ቁጥሮች 1-7 የተገለጹ ክፍያዎች የሚፈጸሙት በፕሮጀክት ሰነዱ ላይ የተፈቀደ የበጀት መስመር ካላቸው ብቻ ሲሆን ሁሉም ክፍያዎች ፈንዱ ወደ ኢንስቲትዩቱ ባንክ አካውንት በገባበት እለታዊ የምንዛሬ ተመን በብር ተከፋይ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 15፡ የውሎ አበል፣ የመጓጓዣ እና ተዛማጅ ወጪዎች**

1. የውሎ አበል፣ የመጓጓዣ እና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች በፕሮጀክት ውል ስምምነት መሰረት የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡
2. በፕሮጀክት ውል ሰነዱ በግልጽ ያልተቀመጠ የውሎ አበል፣ የመጓጓዣ እና ተዛማጅ ወጪዎች እንደ አግባብነቱ በመመሪያ ቁጥር 1118/2018 መሠረት ይፈጸማሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር 2 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ በመንግስት መመሪያ የመኝታ አበል የተፈቀደለት ተቧሚ አመራር ሲሆን መኝታ እስከ አራት ኮከብ ሆቴል እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

ካሪታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

**አንቀጽ 16፡ ህትመት፣ መረጃ ልውውጥና ስርጭት**

1. በፕሮጀክቱ የሚመነጩ መረጃዎችና ህትመቶች የኢንስቲትዩቱና የድጋፍ ሰጪው አካል ኃብት ይሆናሉ። ለነዚህ መረጃዎች ማከማቻ የሚውል ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ይደራጃል። ማንኛውም የፕሮጀክት ተመራማሪ ከፕሮጀክቱ ሥራዎች የሚገኘን መረጃ በዚሁ የመረጃ ቋት ውስጥ በየዓመቱ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።
2. ሕትመቶችን በተመለከተ በፕሮጀክቱ ሰነድ፣ ከድጋፍ ሰጪው አካል ጋር በተገባው ስምምነት እና በተፈጻሚ የተቋሙ የመረጃ እና የህትመት አሰራር መሠረት ይፈጸማሉ።

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**አንቀጽ 17፡ ከመመሪያው ጋር የሚቃረኑ የውስጥ አሰራሮች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም የተቋሙ የውስጥ አሰራር በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**አንቀጽ 18፡ መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

ካርታ ካስኬ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

ቀን: 11 | 10 | 2018 ዓ.ም.